ቀን ታህሳስ 17 2000

**<u>በወቅቱ ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት ለቅንጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተጻፈ ደብዳቤ።</u>**

ለቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤
አዲስ አበባ

እኛ ስማችን ከእዚህ በታች የሰፈረው በወቅቱ ከኢትዮጵያ ውጭ የምንገኝ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት፣ የፓርቲያችን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የላእላይ ምክር ቤት አባላት ስብሰባ በመጥራት ታህሳስ 11 2000 ያስተላለፈው ጥሪ ደርሶናል።

ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በጥሪው በተጠቀሱት የስብሰባ ቀናት በሃገር ውስጥ መገኘት ባንችልም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ላደረገልን ጥሪ የከበረ ምስጋናችንን እናቀርባለን። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በድርጅቱ ህገ-ደንብ መሰረት የቅንጅትን ሥራ ለመስራት እስካሁን ያደረጋቸውንና ወደፊትም የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች በሙሉ ከልብ እንደግፋለን።

ከቅንጅት ድርጅታዊ ህገ-ደንብ በመነሳት የቅንጅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከፍተኛ የሥራ ሃላፊነት የተሸከመና የድርጅቱ የቀን ተቀን ሥራዎች አንቀሳቃሽ ከፍተኛው እርከን መሆኑን እንገነዘባለን። ባለንበት ወቅት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውን ሥራ እንዲያቃልሉ በድርጅቱ ህገ ደንብ መሠረት የተቋቋሙት ኮሚቴዎች በአብዛኛው ሥራ እንዳልጀመሩ እናውቃለን። በተለያዩ ምክንያቶች በርካታ የላእላይ ምክር ቤቱ አባላት ተጉድለዋል። በሃገር አቀፍ ደረጃ የድርጅቱ ጽ/ቤቶች ተዘግተዋል። የድርጅቱን አባለት በቀጥታ ስብሰባ የመጥራት መብት በመንግስት ተገድቧል። ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነቱ እንዳይከበር መንግስታዊ ደንቃራዎች ተጋርጠውበታል። በድርጅታችን ላይ በመንግስትና በጸረ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ከሚሰነዘርበት ጥቃት በተጨማሪ፣ በውስጥ የቅንጅቱ ሊቀመንበርና ጥቂት የአመራር አካለት የድርጅቱን ህገ- ደንብ በመጣስ ጎጂ ተግባራት በሚፈጽሙበት ወቅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተሸከመው ሃላፊነት ከመቸውም በላይ ትልቅና ታሪካዊ እንደሆነ እንረዳለን።

በስበሰባው ጥሪ ላይ እንደተመለከተው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የስራ ድርሻውን ለመወጣት የሚያስፈልገውን ውሳኔ ለማስወሰን የሚችልበትን የላእላይ ምክር ቤት ስብሳባ ጠርቷል። ባለንበት ሁኔታም ቅንጅት ውሳኔ መወሰን የሚችልባቸው እርከኖች የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴውና ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ስልጣንና አቅም በላይ የሆነ ጉዳይ ከተገኘ በላእላይ ምክር ቤቱ ብቻ እንደሆነ እናውቃለን። ከእነዚህ አካላት ውጭ በወቅቱ ሌላ ውሳኔ መስጠት የሚችል አካል የለም። ከእነዚህ ሁለቱ አካለት የበላይ የሆነው አጠቃላይ ጉባኤ ባለንበት ወቅት ሊጠራ የሚችልበት ድርጅታዊ አቅም፣ ዝግጅትና አጠቃላይ ሁኔታ እንደሌለ እንገነዘባለን። በመሆኑም መጪው የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባ ታሪካዊ ትረጉሙ የገዘፈ ይሆናል ብለን እናምናለን።

በእዚህ ስብሰባ አብላጫ ቁጥር ያላቸውን የምክር ቤቱ አበላት እንዲገኙ ለማድረግ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በጥሪው ያሳያውን ጥረት እናደንቃለን። ይህ ሁኔታ ባይሟላም

በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ውሳኔ በማስወሰን ባፋጣኝ መሰራት ያለባቸውን ስራዎች መስራት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴያችን ላይ ወቅቱ የጣለበት ታሪካዊ ግዴታ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህንንም ሃላፊነት በብቃት መወጣት እንደሚችል እናምናለን።

*ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በጥሪው እንዳመላከተው፣ በመጨረሻው የመስብሰብ እድል በመጠቀም በተገኙ የምክር ቤት አባላት አብላጫ ድምጽ የሚወሰንን ውሳኔ ሁላችንም ገዥ አድርጎ እንደሚያየው ያቀረበውን ሃሳብ በሙሉ ልብ እንደግፋለን። በተለይ ባለንበት ወቅት ሥራ አስፈጻሚው በጥሪው ካሰፈረው አካሄድና ሂደት ውጭ ቅንጅት በአፋጣኝ ድርጅታዊ ህልውናውን የሚያስከብርበትም ሆነ ለቀጣዩና በበረካታ ፈተናዎች ለተሞላው የትግል ወቅት እራሱን የሚያዘጋጅበት ሌላ አግባብ እንደሌለው እንረዳለን።*

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የጠራው ስብሰባ ቅንጅትን በሚመጥን የስልጡንነት፣ የዴሞክራሲያዊነት፣ የተጠሪነት፣ የግልጽነትና የአርቆ አስተዋይነት መርሆች በመገዛት፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በድርጅታችን ላይ የጣለውን የአንድነትና የዴሞክራሲያዊ ተስፋ የሚያለመልሙ ውሳኔዎችን በመወሰን በሃገራችን ዴሞክራሲን ለማስፈን የተጀመረውን ጥረት የላቀ ጥራትና ጥንካሬ ወደ አለው አዲስ የትግል ምእራፍ እንደሚያሸጋግረው እንተማመናለን።

በመጨረሻም በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኙ የቅንጅት አበላትና ደጋፊዎች እንዲሁም በሃገራችን ዴሞክራሲ እንዲያብብ የሚፈልጉ አካለት በሙሉ የቅንጀት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የጠራው መጪው የላእላይ ምክር ቤት ስብሰባ የተሳካ እንዲሆን ሁለንተናዊ ድጋፋቸውን እንዲለግሱት ጥሪ እናቀርባለን። እኛም በውጭ የምንገኝ የቅንጅቱ የላእላይ ምክር ቤት አባለት ድርጅታችን ቅንጅት ለህዝብ የገባውን የነጻነት የአንድነትና የዴሞክራሲ ቃል ኪዳን መጠበቅ እንዲችል የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴውና የላእላይ ምክር ቤቱ የሚያደርጉትን ማናቸውንም እንቅስቃሴ በተቻለን አቅም ሁሉ እንደግፋለን። የድርጅታችንንም መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊ ባህሪያትና ዴሞክራሲያዊ ህገ-ደንብ እንዲከበሩ ለማድረግ የሥራ አስፈጸሚ ኮሚቴ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች ጎን በጋራ እንደምንቆም እናረጋግጣለን።

ከምስጋና ጋር

| | |
|---|---|
| ዶር ያቆብ ሃ/ማርያም | የም/ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ከሚቴ አባል |
| አቶ አክሉ ግርግሬ ስራ | ›› ›› ›› ›› ›› |
| ዶ/ር ሙሉአለም ታረቀኝ | ›› ›› ›› ›› ›› |
| አቶ ቸኮል ጌታሁን | ›› ›› ›› ›› ›› |
| ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ | የም/ቤት አባልና የአዲስ አባባ ከተማ ተመራጭ ከንቲባ |
| ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ | ›› ›› ›› ›› ›› ›› ም/ ከንቲባ |
| አቶ አስቻለው ከተማ | የምክር ቤት አባል |
| አቶ ዳንኤል አሰፋ | ›› |
| አቶ መስፍን አማን | ›› |
| አቶ ደበበ እሸቱ | ›› |
| አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ | ›› |